በአላህ መንገድ ወጪ ካደረግከው አንድ ዲናር፤ ባሪያ ነፃ ለማውጣት ወጪ ካደረግከው አንድ ዲናር፤ ለሚስኪን ምፅዋት ካደረግከው አንድ ዲናር፤ ለቤተሰቦችህ ወጪ ካደረግከው አንድ ዲናር መካከል ትልቅ ምንዳ የሚያስገኘው ለቤተሰብህ ወጪ ያደረግከው ነው።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ
(የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "በአላህ መንገድ ወጪ ካደረግከው አንድ ዲናር፤ ባሪያ ነፃ
ለማውጣት ወጪ ካደረግከው አንድ ዲናር፤ ለሚስኪን ምፅዋት ካደረግከው አንድ ዲናር፤ ለቤተሰቦችህ ወጪ ካደረግከው አንድ ዲናር
መካከል ትልቅ ምንዳ የሚያስገኘው ለቤተሰብህ ወጪ ያደረግከው ነው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አንዳንድ የምፅዋት አይነቶችን እንዲህ በማለት አወሱ። "በአላህ መንገድ ለሚደረግ ትግል ወጪ ያደረግከው አንድ ዲናር፣ ከባርነት ነፃ ለማውጣት ወጪ ያደረግከው አንድ ዲናር፣ የሚያስፈልገው ለሆነ ሚስኪን ወጪ ያደረግከው አንድ ዲናር፣ ለቤተሰብህና ለዘመዶችህ ወጪ ያደረግከው አንድ ዲናር ይኖራል።" ቀጥለውም ከነዚህ መካከል አላህ ዘንድ ትልቅ ምንዳ የሚያስገኘው ዲናር ቀለብ ግዴታ ለሆነብህ የቤተሰብ አካል የምታወጣው ወጪ እንደሆነ ተናገሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5813